ተዛማጅ ደንቦችና መመሪያዎች፡- **ABC, ACA, COA, IEA, IKA, IKA-RA, JEA-RA**

ኃላፊነት ያለው ቢሮ፡- ዋና የአካደሚክ ኦፊሰር ጽ/ቤት፣ የስርዓተ ትምህርት እና ትምህርታዊ ፕሮግራሞች ጽ/ቤት **Office of the Chief Academic Officer; Office of Curriculum and Instructional Programs**

## የቤት ሥራ

**A.** ዓላማ

1. ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ስለሚሰጣቸው የቤት ሥራ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህር ቦርድ ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ለማዘጋጀት

2. ቦርዱ ለተማሪዎች አካደሚያዊ፣ ማህበራዊ-ስሜታዊ እና አካላዊ እድገት እና ደህንነት ካለው ለረጅም ጊዜ ከቆየ ቁርጠኝነት እና ከጠንካራ የአካደሚክ ፕሮግራም ጋር ለሚጣጣሙ ምክንያታዊ ለሆኑ የቤት ስራ ልምዶች መመሪያ ለመስጠት

3. ከቦርዱ ቁርጠኝነት እና በጥናት ላይ ከተመሰረቱ ምርጥ ተሞክሮዎች ጋር በሚጣጣም መልኩ የትምህርት ዓላማዎችን ለማሳካት ሆን ተብሎ የተነደፈውን የቤት ስራ አስፈላጊና ጠቃሚ መሆኑን ለማረጋገጥ ~~ለተማሪ የሚሰጥ የቤት ስራ በተማሪው(ዋ) አጠቃላይ ፕሮግራም ውስጥ አስፈላጊ እና ጠቃሚ ተደርጎ እንደሚቆጠር በድጋሚ ለማረጋገጥ~~

**B.**ጉዳዩ

በቤት ውስጥ የሚጠናቀቁ የተማሪዎች የቤት ስራዎች ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው እንዲሰሩ የግል ብስለትን፣ ተፈላጊ ተግባሮችን በግልጽ መረዳትን/መገንዘብን፣ እና ለማጥናት ምቹ የሆነ አካባቢን ጨምሮ ድጋፍ ሰጪ መገልገያዎች/ግብዓቶች ያስፈልጋሉ። የቤት ስራ ቤተሰቦች ተማሪው(ዋ) በትምህርት ቤት ስላለው/ስላላት ተሞክሮ ያላቸውን ግንዛቤ ለማጠናከር እድል ይሰጣል።

በቤት ውስጥ ራሳቸውን ችለው የሚሰሩ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እድሜ ላይ ያሉ ተማሪዎች ከህሎታቸውን

ለማዳበር ሆን ተብሎ ሲነደፍ ዋጋ እንዳለው ይታወቃል። ብስለታቸው እየጨመረ/እያደገ በሄደ ቁጥር፣ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች እያደገ የሚሄድ ራስን የመቻል ዝንባሌ ይኖራቸዋል፤ እና ራስ-መር ከሆኑ የመማር እድሎች ተጠቃሚ ይሆናሉ። የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እድሜ ላይ ላሉ ተማሪዎች የሚሰጥ የቤት ስራ ከትምህርት ቤት አደረጃጀት ውጭ ከሚከሰቱት ሌሎች ስራዎች/ተግባሮች ያነሰ ቀዳሚ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ እንደሆነ ጥናቶች ያመለክታሉ። ነገር ግን፣ ራስን ለማዝናናት ተብሎ በእድሜ ከሚያንሱ ተማሪዎች ጋር የሚደረግ በቤተሰብ የተደገፈ ዕለታዊ ምንባብን ወጥ በሆነ መልኩ መተግበር ጠቀሜታ እንዳለው የተረጋገጠ ነው።

**C.** አቋም

1. የቤት ስራ ቦርዱ ለተማሪዎች [1] አካደሚያዊ፣ ማህበራዊ-ስሜታዊ እና አካላዊ እድገት እና ደህንነት ካለው ቁርጠኝነት ጋር መጣጣም አለበት።

    a) የቤት ስራ ፍትሃዊ እና ትርጉም ያለው የተማሪ ስራ ነጸብራቅ/ማሳያ መሆን አለበት። የቤት ስራ የሌሎችን ድጋፍ ምን ያህል እንደሚፈልግ፣ ወይም የሌሎችን ስራ እንደሚያንጸባርቅ፣ የተማሪን የመማር ደረጃ ለመገምገም ጥቅም ላይ የሚውል ከሆነ ለቤት ስራ መሰጠት ያለበትን ዋጋ ይቀንሳል።

    b) ተማሪዎች በ MCPS የትምህርት ፕሮግራም ውስጥ በሚያደርጉት ተሳትፍ ላይ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ተግባሮችንና ልምዶችን ለመለየት እና አማራጮችን ለማዘጋጀት የቤት ስራ ተሞክሮዎች በጥልቀት መፈተሽ አለባቸው።

        c) የቤት ስራ ትግበራዎች ተማሪዎች ከትምህርት ቤት የሚሰጣቸውን ስራዎች ለመሥራት እና ለማጠናቀቅ የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ ሰጪ መገልገያዎችን/ግብዓቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት ሆን ብሎ የተነደፉ መሆን አለባቸው። ግላዊ ሁኔታን መሠረት ተደርጎ የተዘጋጁ የትምህርት ፕሮግራሞች ወይም **504** ፕላን ያላቸው ተማሪዎች የተሰጣቸውን ተግባሮች ለማጠናቀቅ የሚያስፈልጉትን አስፈላጊ መገልገያዎች ማመቻቾቶች እና

[1] የሚከተሉትንም ይመልከቱ፡- የቦርድ ፖሊሲ ABC፣ *የቤተሰብ እና የትምህርት ቤት አጋርነት*፣ ፖሊሲ ACA፣ *ከአድሎ-ነፃ የሆነ፣ ፍትሃዊነት/ሚዛናዊነት፣ እና ባህላዊ ብቃት/እውቀት ማስፈን*፣ ፖሊሲ IEA፣ *ቀደምት የህጻንነት/የልጅነት እና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማዕቀፍ*፣ፖሊሲ IEB፣ *የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት*፣ፖሊሲ IED፣ *የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ማዕቀፍ እና መዋቅር*፣ ፖሊሲ IKA፣ *ውጤት አሰጣጥና ሪፖርት አቀራረብ*፣ እና ፖሊሲ JPG፣ *ደህንነት፡ የአካላዊ እና የአመጋገብ ጤንነት*.

አጋዥ ቴክኖሎጂ እና ተደራሽ ፎርማቶችን የመሳሰሉ ተጨማሪ እርዳታዎችን እና አገልግሎቶችን ማግኘት አለባቸው።

d) በሚቻልበት ጊዜ፥ አስተማሪዎች የቤት ስራዎችን ከተመሳሳይ የተማሪ ቡድን ወይም በተለያዩ **የትምህርት ዓይነቶች ውስጥ ካሉ ሌሎች አስተማሪዎች ጋር ማቀናጀት እና ፣የተማሪን ደህንነት መጠበቅ አለባቸው።**

e) ተማሪው(ዋ) ሃይማኖታዊ በዓላትን ለማክበር የሚቀር/የምትቀር ከሆነ ላመለጠው/ላመለጣት ስራ ዝግጅት ማድረግ እንዲቻል ተማሪዎች እና ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው ለተማሪው(ዋ) መምህር በቅድሚያ እንዲያሳውቁ ይበረታታሉ። ከትምህርት ቤት መቅረቱ(ቷ) ተቀባይነት ካገኘ/ከተፈቀደ፣ ተማሪው(ዋ) በትምህርቱ(ቷ) እንዲቀጥል/እንድትቀጥል እንደ አስፈላጊነቱ ተማሪው(ዋ) ያመለጠውን/ያመለጣትን ስራ ለማካካስ መምህሩ(ሯ) አማራጮችን ይሰጣል/ትሰጣለች።

**2.** ዓላማ ያለው ትልም

የቤት ስራዎች ከሚሰጡት ትምህርቶች ዓላማ ጋር በቀጥታ የተያያዙ መሆን አለባቸው።

a) **ትርጉም ያለው ትምህርት የተማሪዎችን የማሰብ/የማገናዘብ ችሎታ ይገዳደራል፣ ተማሪዎች ግምቶቻቸውን/በማስረጃ ያልተደገፉ ድምዳሜዎቻቸውን እንዲፈትሹ ያበረታታል፣ እና የፕሮብሌም አፈታት ክህሎትን ያዳብራል። በጥልቀት እንዲያስቡ ማድረግ ከተሰጠው የቤት ስራ ብዛት ጋር መምታታት የለበትም።**

b) መምህሩ(ሯ) የስርዓተ ትምህርት ዓላማዎችን ለማሳካት የቤት ስራን ዓይነት፣ ድግግሞሽ እና ርዝማኔ በተሻለ ሁኔታ ሊወስን/ልትወስን ይችላል/ትችላለች፣ ይህም እንደ አመቺነቱ እና እንደ አግባብነቱ፣ ትምህርት በሚሰጥበት ጊዜ ተማሪዎች ለቤት ስራ ድጋፍ እንዲጠይቁ ዕድል መስጠትን ሊያካትት ይችላል።

c) መምህራን የቤት ስራን ንድፍ ማዘጋጀት ያለባቸው –

(1) ተማሪዎች ስለ ቤት ስራው እና ስለ ዓላማው ግልጽ ግንዛቤ አእንዲኖራቸው፣

(2) **ትርጉም ያለው የቤት ስራ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት እንዲያሟላ እና እንዲያዳብር/እንዲያበለፅግ፣ እና**

(3) የሚሰጡት የቤት ስራዎች ብዛት እና የሚሰጡበት ጊዜ ለተማሪዎች እድሜ ተመጣጣኝ እና አግባብ በሆነ መልኩ ይሆናል።

(a) በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት እና በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በሚማሩበት አመታት፣ተማሪዎች በቤት ውስጥ ራሳቸውን ችለው ለመስራት ብስለት ሲኖራቸው ስርዓተ ትምህርቱ እና ተዛማጅ የቤት ስራ ተግባሮች ተማሪዎች በጥልቀት እንዲያስቡ በማድረግ ረገድ ጠንከር ይላሉ።

(b) ለአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የሚሰጥ **ማንኛውም** የቤት ስራ እድሜአቸውን የሚመጥን እና አንድ የአንደ ደረጃ ት/ቤት ተማሪ ራሱን ችሎ ሊያጠናቅቃቸው የሚችላቸውን ተግዳሮቶችን ብቻ መሆን አለበት።

**d) በተጠናቀቁ የቤት ስራዎች ላይ የሚሰጥ ግብረመልስ ተማሪዎችን በተጨማሪ የትምህርት ተግባራት ላይ የሚረዱ/የሚያበረታቱ እና መምህሩ(ሯ) ትምህርታዊ ክትትልን እንዲያቅድ/እንድታቅድ የሚረዳ መሆን አለበት።**

~~የእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ትምህርታዊ እቅድ እያንዳንዱ ልጅ በመሠረታዊ ክህሎቶች የተሟላ እና ስልታዊ መሰረታዊ ትምህርት ማግኘቱ(ቷ)ን ለማረጋገጥ የትምህርት ቤቱን ሃላፊነት ለመወጣት ትምህርት ቤቱ እና እያንዳንዱ አስተማሪ የቤት ስራን በአግባቡ የሚጠቀሙበት መንገድ ላይ ትኩረት ማድረግ አለበት።~~
~~ከመዋእለ ህጻናት (K) እስከ-8ኛ ክፍል የቤት ስራ በሳምንት ከሰኞ እስከ አምስት ጊዜ መሰጠት አለበት፤ እና የዕለት ተዕለት መደበኛ ተግባር/አሰራር ተደርጎ መወሰድ አለበት።~~
~~የቤት ስራ ተግባራት በግምገማ እና በልምድ ማዳበር ፅንሰ-ሃሳብን እና ክህሎትን ለማሳደግ እድል መስጠት አለባቸው። ውበትን ማድነቅ ወይም ማህበረሰብን እና የተፈጥሮ ሃብቶችን ማድነቅ እና አጠቃቀምን የሚያካትቱ ተግባራት ጭምር ተገቢ የቤት ስራዎች ይሆናሉ።~~

~~የተጠናቀቁ የቤት ስራዎች በመምህሩ(ሯ) (ወይም ተወካይ) መገምገም አለባቸው እና ተገቢው -ትምህርታዊ ክትትል መደረግ ይኖርበታል።~~

3. ግንኙነት

a) ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ተማሪዎች በእያንዳንዱ የትምህርት ዓመት መጀመሪያ (በተጨማሪም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሦስተኛው የማርክ መስጫ ወቅት) አግባብነት ስላላቸው የቦርድ ፖሊሲዎች፣ እና የትምህርት ቤት እና የትምህርት ክፍል የቤት ስራ ሂደቶች መረጃ ይሰጣቸዋል።

~~ሴፕቴምበር ላይ እና (በማርች ወር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች) ካውንቲው፣ ትምህርት ቤት እና የትምህርት ክፍሉ ስለ ቤት ስራ ያላቸውን መመሪያ/ደንብ/ፖሊሲ ለወላጆች እና ለተማሪዎች ማሳወቅ አለባቸው።~~

b) የተለያዩ ውጤታማ፣ አካታች፣ ለተማሪዎች ባህል እውቅና እና ዋጋ የሚሰጡ እና ከዘረኛነት የፀዳ የመግባባት ስልቶች ቤተሰቦች የመማርን ጥቅም እና የሚሰጡ ኮርሶችን አላማዎችን እና የቤት ስራዎችን እንዲያገኙ እድል ይሰጣቸዋል።

4. ተማሪዎች ት/ቤት ሳይመጡ ቀርተው በሚመለሱበት ጊዜ መምህራን ተመጣጣኝ፣ ግን የተለየ ስራ ወይም ተግባር ሊሰጧቸው ይችላሉ። የተማሪዎች ከት/ቤት መቅረት ህጋዊ ቢሆንም/ባይሆንም ተማሪዎች ያመለጣቸውን የትምህርት ስራዎች ማካካሳቸው አስፈላጊ ነው።

~~ተማሪ ከትምህርት ቤት ጋር በተያያዙ በሌሎች ተግባሮች ምክንያት ሲቀር/ስትቀር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የቤት ስራ በአስተማሪ ድጋፍ- ሊካካስ ይችላል።~~

D. ተፈላጊ ውጤት

1. የቤት ስራ የሚከተሉትን ማሟላት አለበት –

a) **ትምህርታዊ ፕሮግራምን ለመደገፍ ሆን ተብሎ የተነደፈ እና ቦርዱ ለተማሪዎች አካደሚያዊ፣ ማህበራዊ-ስሜታዊ እና አካላዊ እድገት እና ደህንነት ካለው ለረጅም ጊዜ የቆየ ቁርጠኝነት ጋር መጣጣም፣ እና**

**b) ራሳቸውን የቻሉ እድሜያቸውን በሙሉ በራሳቸው ተነሳሽነት እውቀትን እና ክህሎትን ቀጣይነት ባለው መልኩ የሚያሳድጉና የሚያበለፅጉ ተማሪዎችን የትምህርትና የእውቀት እድገት ማዳበር።**

**2. የቤት ስራ በጥናት ላይ ከተመሰረቱ ምርጥ ተሞክሮዎች ጋር መጣጣም አለበት።**

**F. የትግበራ ስልቶች**

**1. የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ለሁሉም ተማሪዎች ተደራሽ የሆነ ዓላማ ያለው፣ ፍትሀዊ የሆነ የቤት ስራ ልምዶችን እናከምርምር/ከጥናት እና ከምርጥ ተሞክሮዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ ለአስተማሪዎች ሙያዊ የትምህርት እድሎችን ለመተግበር አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን ወይም ሌሎች አስተዳደራዊ ሂደቶችን ያዘጋጃል/ታዘጋጃለች።**

~~የቤት ስራዎች በአስተዳደራዊ መመሪያና ደንብ መሰረት ከትትል ሊደረግባቸው ይገባል።~~

2. ትምህርት ቤቶች ስር የሰደደ የቤት ሥራ አለመጠናቀቅ ድግግሞሽ ላይ የሚከተሉትን ግምት ውስጥ ያስገባ መሰረታዊ መንስኤዎችን ትንተና ያከናውናሉ/ያደርጋሉ –

a) እንደገና/ደግሞ ማስተማር፣ ማሰልጠን ወይም ተማሪዎች የቤት ስራዎችን እንዲያጠናቅቁ አስፈላጊ ሊሆን የሚችል ሌላ ድጋፍ መስጠት፣

b) ለትምህርት ቤት የደህንነት ቡድኖች ወይም ለትምህርት አስተዳደር ቡድኖች ማሳወቅ ያለባቸው የግለሰብ ተማሪ ፍላጎቶች፣ ስጋቶች፣ ወይም ሁኔታዎች፣ እና

c) ለጥናት ምቹ የሆኑ እና ለተማሪዎች ተደራሽ የሆኑ አካባቢዎች፣ እና አስፈላጊ የሆነ ቴክኖሎጂ እና ሌሎች አጋዥ መገልገያዎች/ግብአቶች ተደራሽነት እንዲኖራቸው እና የታለመለትን ተግባር ለማከናወን አመቺ ሁኔታ ማዘጋጀት።

~~የቤት ስራዎች ሲሰጡ ከፍል ውስጥ በተማሪዎች መካከል ያለውን ልዩነት ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው።~~

F. ግምገማ እና ሪፖርት

ይህ ፖሊሲ በትምህርት ቦርድ የፖሊሲ ግምገማ ሂደት መሰረት ~~ቀጣይነት ባለው መልኩ~~ በየሶስት ዓመቱ ይገመገማል።

~~ተዛማጅ ምንጮች፡-~~

የፖሊሲው ታሪክ፡- በውሳኔ ቁጥር 76977 የፀደቀው ኖቬምበር 8,1977፣ በውሳኔ ቁጥር 33386፣ ጁን 12, 1986፣ እና በውሳኔ ቁጥር 45886፣ ኦገስት 12,1986 መሰረት አቀራረቡ ተስተካክሏል፣ በውሳኔ ቁጥር 51786፣ ሴፕቴምበር 22,1986 ተቀባይነት አግኝቷል፣ የተሻሻለው____፣ በውሳኔ ቁጥር _____።